Alcohol and Drug Problems Happen in All Kinds of Families
Amharic

# የአልኮልና የእፅ ችግሮች በተለያዩ ቤተሰብ ውስጥ ይከሰታሉ

በአስቸጋሪ ወቅት ፍቅርን መደጋገፍን እና ምክርን የሚጋራ ቤተሰብ ሲኖር ማንኛውንም ችግር መቋቋም ቀላል ይሆናል:: ሆኖም ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች የሚፈቃቀር ቤተሰብ ቢኖርም ችግርን ለማስወገድ እርዳታ የግድ ያስፈልጋል ለዚህም ተጠቃሽ ምሳሌዎች እፅና የአልኮል ችግሮች ናቸው::

አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ችግሮች የሚያጠቁት የተወሰኑ ዓይነት ቤተሰቦችን ነው ብለው ይገምታሉ የሚያጠቁት ግን በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉና የተለያዩ ኃይማኖት ተከታዮች ቤተሰቦችንም ጭምርም ነው:: ለምሳሌም የ48 ዓመት አስተማሪ የሆነችውን ካርላንም አጥቅቷታል:: ካርላ በየዕለቱ ማልዳ በመነሳት የእፅ ሱሰኛ የሆነውን የ22 ዓመት ልጇን ቶኒን ወደሥራው እንዲሄድ ለመቀስቀስ ወደ ሚኖርበት ቤት በመኪናዋ መሄድ ግድ ሆኖባታል:: ካልሆነ ከሥራው ይፈናቀላል::

በሳምንት 5 ቀን ይኼንን ማድረግ ለካርላ በጣም ከባድ ነው:: ቶኒን ለመቀስቀስ ረጅም ጊዜ ስለሚወስድባት እሷራሷም አልፎ አልፎ ወደ ሥራዋ የምትደርሰው ዘግይታ ነው:: ባለቤቷ ከሰማ እንደሚቆጣ ስለምታውቅ ጉዳዮን የምታከናውነው በሚስጥር ነው:: ስለልጃቸው የእፅ ችግርም አውግዟታል:: አዘውትሮም «ገና ልጅ ሳለ ገስፀሽው ቢሆን ኖር እንደዚህ አይሆንም ነበር» ይላታል::

የኋላ ኋላም ካርላ ለመጀመሪያ ጊዜ በማህበረሰቡ ጤና ጣቢያ ውስጥ ያለውን ጉዳዩ የሚመለከተውን ሰው አግኝታ በማማከሯ ትንሽ እፎይታን አገኘች አማካሪውም ልጇን በምን ዓይነት መንገድ እንደምትረዳው ተጨማሪ ዕርዳታና ምክር ለገሣት::

እያሌ ሰዎች፣ ካናዳዎች ስለግል ችግራቸው ከአማካሪ ጋር መወያየት እንግዳ ነገር ሆኖባቸው:: ይኼም የቱን ያህል እንደሚረዳ አልተገነዘቡትም ማለትም ካርላ እንደተረዳችውና ችግርችን ለማቃለል እንደጠቀማት ሁሉ::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ችግሮቻቸውን በተለይም ከአልኮልና ከእፅ ጋር የተያያዙትን ከቤተሰቦቻቸው ውጪ ለመወያየት ያሳፍራቸዋል:: ማንኛውንም ከአደንዛዥ (ማለትም እፅ አልኮል....) ጋር የተያያዘን ችግር አምቆ መያዝ ሱሰኝነቱ እንዲቀጥል ከማድረጉም ባሻገር ለተጠቃሚውም ሆነ ለቤተሰቡ የበለጠ አስከፊ ችግር ያስከትላል:: የእፅና የአልኮል ችግሮች የጤና ቀውስ ያስከትላሉ ስለሆነም እንደማንኛውም የጤና ችግር የባለሙያ ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል::

ሰለጉዳዩ የምታነጋግረው አማካሪም ሆነ ሌላ የጤና ባለሙያ ከአንተ ፍላጉት ውጭ ችግርህን ለ3ኛ ሰው አሳልፎ ማሳወቅ የለበትም:: የቤተሰብ አባላትንም ጨምር ለማንኛውም ሰው እንዳይናገሩ ሕጉ በጥብቅ ይከለክላቸዋል:: ሪፖርት ማድረግ የሚቻለው የሚከተሉት ምልክቶች የታዩ ጊዜ ብቻ ነው:: 1. ራስን የመጉዳት አዝማሚያ 2. ሌሎችን የመጉዳት አዝማሚያ 3. ሕፃናትን የማጥቃት 4. ሽማግሌዎችን የማጥቃት አዝማሚያ:: እነዚህ ጥብቅ ሕጉች አስተርጓሚዎችንም ይመለከታሉ:: አስተርጓሚ አስፈልጉህ የምታውቀው ሰው ከሆነ ሌላ አስተርጓሚ እንዲመደብልህ መጠየቅ ትችላለህ::

የእፅና የአልኮል ግልጋሎቶች በብዙ የተለያዩ መንገዶች ይረዳሉ መረጃ በመስጠት፣ በማማከርና በሕክምና እና ወደ ሌላ አገልግሎት ወደ ሚገኝበት በመምራት ዕርዳታ የሚያስፈልግህ ከሆነ ወደ ማህበረሰቡ ጤና ጣቢያ በመደወል ምን አይነት እርዳታ ማግኘት እንደምትችል ማወቅ አለብህ ለጥያቄህ ምላሽ በፍጥነት ካላገኘህ የስልክ ቁጥርህን በመተው እንዲደውሉልህ ማድረግ ወይም ዘግይተህ መደወል ይጠበቅብሀል::

The material in this brochure has been adapted from documented by NSW Multicultural Health Communication Service.
This brochure can be reproduced as required.

Canadian Mental Health Association – Edmonton Region Phone: (780) 414.6300 www.cmha-edmonton.ab.ca
Edmonton Mennonite Centre for Newcomers Phone: (780) 424.7709 www.emcn.ab.ca
Multicultural Health Brokers Co-op Phone: (780) 423.1973